# <u>ምን ያደርጋል...</u>

በእንዶድ የታሸው፣
የነጣው ልብሳቸው
ኣምሮ፣ ተተኩሶ
ሱሪና ኮታቸው፣
    ታድያ ምን ያደርጋል...
ለጉድ ይታያሉ ሲሄዱ ዕርቃናቸው!

ምን ዓይነቱ ውሎ
ከትሮም፣ ጥብስም ሞልቶ
ከነ ኣይመሎ
ቁርጥም ተጐልቶ
    ታድያ ምን ያደርጋል...
የሚበሉት ቆሎ፣ ጾመኞች ናቸው?

የዛሬ ኣርበኞች
ማማሩ ትጥቃቸው፣
መቶ ሓምሳ ጥይት
ሞልቶ ዝናራቸው
    ታድያ ምን ያደርጋል
ባዶ ነው እጃቸው፣ ጠመንጃም የላቸው!

ሚዶው፣ ማበጠርያው፣
ሁሉም በየዓይነቱ
የጸጉር ቅባቱ
ኦረ ስንቱ፣ ስንቱ
    ታድያ ምን ያደርጋል...
ኣንድም ጸጉር የለው፣ መላጣው ራሳቸው!

**ገ/ኢ. ጐርፉ።**